## በፌስ-ቡክ መድረካችን ላይ
## በሰኔ ወር፥ ፳፻፰ ዓ. ም. ለቀረቡ ጥያቄዎችና ትችቶች፡
## ከኢእመ የተሰጡ መልሶች።

**ከDeneke Tadesse የቀረበ አስተያየት፡-**

*ዘሀገረ ብህንሳ:- ብህንሳ እራሷ የግብጽ ከተማ ናት።*

*ይህ የቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮ አይመስልም፤ በግልፅ አባባል ማስረዳት ይቻል ይሆን?*

**ከኢእመ የተሰጠ መልስ፡-**

ይድረስ፡- ለአቶ ደነቀ ታደሰ!

ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በእግዚአብሔር አብወእም ስም እያቀረብንልዎ፥ ደግሞም፡ መልስ ስለሰጠንበት፡ ስላለፈውም ኾነ፡ ስለአኹኖቹ ትችቶችዎ፡ "እግዜር ይስጥልን!" እያልንዎ፡ ምላሻችንን፡ እንደሚከተለው አሥፍረንልዎታለን።

፩ኛ፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ፡ እርስዎ፡ "የግብፅ ከተማ ናት!" ያሏት፡ ሀገረ-ብህንሳ፡ እንደሌሎቹ የዓለም ከተሞች ኹሉ፡ እርሷ ጭምር፡ ኹሉን ፈጥራ በባለቤትነት በያዘችው፥ በመላው የሰማይና የምድር ፍጥረተ-ዓለማትም ላይ በሰፈነችው፡ በዘለዓለማዊቷ አገራችን፡ በኢትዮጵያ ድንግል ማርያም የታቀፈች ናት።

፪ኛ፡ እርስዎ፡ "ቤተ-ክርስቲያናችን" የሚሏት፡ እርሷ፡ የዛሬ ፩ሺ፮፻ ዓመት፡ በ፬ኛው የክርስትና ምእት-ዓመት ላይ፡ በግብፃውያን መነኮሳት፡ በኢትዮጵያ ምድር እንደተቋቋመች፡ ራሷ አምና፡ ሌሎችንም ለማሳመን የምትጥረውን፤ ራሷን፡ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን" ብላ የምትጠራውን ከኾነ፥ ይህችው ቤተ-ክርስቲያን፡ **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ የምትታወቀው፡ "በኢትዮጵያ፡ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቅርንጫፍ" ተብላ መኾኑን፡ በቅድሚያ፡ ይህን እውነታ እንዲገነዘቡት ልናሳስብዎ እንወድዳለን።

በመቀጠል ደግሞ፡ ሊያውቁት የሚገባዎን እውነታ እንግለጥልዎ፡- **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ዘንድ፡ ከፍጥረተ-ዓለም ጀምሮ ያለውንና ፍጹም የእግዚአብሔር ብቻ የኾነውን፡ እውነተኛውን ዘለዓለማዊና ክህነታዊ የአስተምህሮ ተልእኮዋን፡ እነሆ እስካኹን፡ ለ፯ሺ፭፻፰ ዓመታት እያበረከተች ያለችው፡ "የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን" ተብላ የታወቀችው መኾኗን ነው። እርሷም፡ መንፈሳዊዉን አገልግሎት፡ ለሕዝቧ እንዲያበረክት፡ በቤተ-ሕዝቧ የተሠየመው፡ ራሷ፡ ቤተ-ክህነቱ ናት። ሥጋዊዉን አገልግሎት፡ ለሕዝቧ እንዲያቀርብ፡ በቤተ-ሕዝቧ እንደተሠየመው፡ እንደቤተ-ምልክናው ዘርፍ ማለት ነው።

እንዲህ፡ በእርስዎና በመሰሎችዎ ዘንድ፡ ሊኖር ለሚችለው፡ ለዚህና ለሌላው፡ እጅግ ብዙ ለኾነው፡ እንደዚህ ላለው፡ የተያያዘ ጥያቄና ትች ኹሉ፡ አጥጋቢ መልስና በቂ ማብራሪያ ኾኖ፡ በጽሑፍ የተሰጠው ዝግጅታችን፡ በኀዋ ሰሌዳችን፥ እንዲሁም፡ በፌስ ቡክ፥ በዩ-ቲዩብና በሳውንድ መድረኮቻችን፥ ዝርዝራቸውም፡ በእነርሱ ላይ ሠፍሮ በሚነበበው መጽሓፎቻችን ውስጥ ስለሚገኝ፡ እባክዎ ያንን ይመልከቱ!?

ይህን የጨዋነት ምግባር በመፈጸም፡ የእርስዎንና የእኛን ውድ ጊዜ ማዳን ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ ጋር፡ በእርግጥ፡ ስለእግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት እውነት፡ የማወቅ ፍላጎት ካለዎ፥ ያም ፍላጎትዎ፡ እውነተኛ ከኾነ፡ ያን ፍላጎትዎን፡ በዚያ ምግባርዎ፡ በበለጠ ሊያረኩት ይችላሉ።

\+ \+ \+

ከTewodros Hunachew **የቀረበ አስተያየት፦**

*ሙሽሪት፦ ሚስት በሚለው ባይትረጎም (መመረጥ ብንለው) አለማዊ ዕሳቤ እን[ዳ]ይዝ።*

**ከኢእመ የተሰጠ መልስ፦**

ይድረስ፦ ለአቶ ቴዎድሮስ ኹናቸው!

ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በእግዚአብሔር አብወእም ስም እያቀረብንልዎና ስለአስተያየትዎ፡ "እግዜር ይስጥልን!" እያልንዎ፡ መልሳችንን፡ እንደሚከተለው እናበረክትዎታለን።

እግዚአብሔር እም [እናት]፡ ከእግዚአብሔር አብ [አባት] ጋር ያላት የአንድነት ግንኙነት፡ "ሚስት" በሚለው ቃል እንዳይተረጎም የፈለጉት ለምንድር ነው? ይኸው "ሚስት" የሚለው፡ ቅዱሱና ንጹሑ መለኮታዊ ቃል፡ እንደእርስዎ ዘይቤና አጻጻፍ፡ ***"አለማዊ ዕሳቤ እን[ዲ]ይዝ"*** ለምንና በማንስ ተደረገ? በመሠረቱ፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብሩ፡ ከየት የመጣ ይመስልዎታል?

መቸም፡ በምድር ላይና በሰዎች መካከል፡ ጥንትም፥ በአማካዩ ዘመንም፥ ዛሬም፥ ወደፊትም፥ ለዘለዓለምም፥ ምንጊዜም፡ የእግዚአብሔርን እውነት ገላልጣ የምታብራራና የዲያብሎስን ሓሰት አጋልጣ የምታወጣ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ብቻ ናትና፡ አኹንም፡ ለእርስዎ ትች፥ ከላይ ለተመለከቱትም ጥያቄዎች፡ ባጭሩ፡ የምትሰጠውን መልስ ይስሙ!

ከኹሉ አስቀድሞ ሊያውቁት የሚገባዎ እውነታ፡ ጋብቻ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ ያ፡ ጾታ ያልነበረው፡ አንድ ፈጣሪና አምላክ የኾነው እግዚአብሔር፡ መጀመሪያ፡ ራሱን፡ "እግዚአብሔር አብ" በሚል፡ በወንድነት [በባልነት] እና "እግዚአብሔር እም" በሚል፡ በሴትነት [በሚስትነት] ጾታ፡ ከኹለት ከከፈለ በኋላ፡ ልጁን፡ እግዚአብሔር ወልድን ለማስገኘት፡ የሠራውና ራሱ የፈጸመው፡ መለኮታዊ ሥርዓት መኾኑን ነው።

ይኸው፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብር፡ ልክ፡ በዚያው በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት መልክና ይዘት፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያው፡ የፍጥረተ-ዓለም ጊዜ፡ ለፈጠራቸው አዳምና ሔዋን ከሰጣቸው፡ የአንድነት ህልውና ሥርዓት፡ የተገኘ ነው።

ታዲያ! እንዲህ ካልኾነ፡ ለምን፡ "ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ንግበር ሰብአ፡ በአርአያነ፥ ወበአምሳሊነ!

"ወገብሮ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በአምሳለ-እግዚአብሔር። ተባዕተ፥ ወአንስተ፡ ገብሮሙ። ወባረኮሙ እግዚአብሔር፤ ወይቤሎሙ፡- 'ብዝኁ! ወተባዝኁ! ወምልእዋ ለምድር! ወቅንይዋ!

"ወይቤ እግዚአብሔር፡ 'ናሁ አዳም ኮነ፡ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ ያእምር ሠናየ፥ ወእኩየ።"

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'ሰውን፡ በመልካችንና በአምሳያችን እንፍጠር!' ይህንም ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የሕያዋን-እናት-ልጅን፡ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረ። ወንድ እና ሴትም አደረጋቸው። 'ብዙ! ተባዙም! ምድርንም፡ ሙሏት! አቅኗትም!'

"እግዚአብሔርም አለ፡- 'እነሆ፡ አዳም፡ መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ፡ ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!" ተብሎ ተነገረ፤ ተጻፈም? እውነታው፡ ይህ ስለኾነ ነው። (ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.፡ ፩፥ ፳፮-፳፰፤ ፫፥ ፳፪።)

እውነታው ይህ ከኾነ፡ ታዲያ! ይኸው፡ "ባልና ሚስት" የሚለው ስያሜና ግብር፡ ለምን፡ እንደነውር፥ እንደጸያፍና እንደዓለማዊ ተቆጥሮ፡ አንድ ልጃቸውን እግዚአብሔር ወልድን ላስገኘውና እግዚአብሔር እም፡ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ላላት የአንድነት ግንኙነት፡ "ሚስት" የሚለው፡ የተቀደሰና ንጹሑ መለኮታዊ ቃል እንዳይውል ተፈለገ?

እንዲህ እንዳይውል የተፈለገው፡ እግዚአብሔር ፈጥሮ የሠራውን፡ ራሱን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን ጋብቻ፥ በእርሱም አማካይነት፡ የሚፈጸሙትንና እውን የሚኾኑትን፡ የቅድስናውንና የንጽሕናውን ምግባራት፡ ክፉ ሰዎች፡ በክፉው አስተሳሰባቸው፡ ወደሰይጣናዊነት እንዲለወጡና እንዲማስኑ በማድረጋቸው፥ ለዝንተ-ዓለም ሲካኼዱ የኖሩትን፡ ይህንኑ የጥፋት ዘመቻቸውንም፡ ከግብ ለማድረስ በመፈለጋቸው መኾኑን፡ አጋልጦ ማሳወቅ ይገባል።

ይህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ ከዚህ የሚከተሉትን የሓሰትና የክፋት ድርጊቶች፡ በጥቂቱ መጥቀስ ይቻላል፡-

-በወንዱ አካለ ሥጋ ውስጥ፡ በእግዚአብሔር መልክና "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾነ!" የተባለለትን፡ ሰውን የሚያህል ፍጡር የሚያስገኘውን፥ደግሞም፡ ፈጣሪ፡ በልዩ ጥበቡ የሠራውን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን ዘር፡ "ኃጢኣት" ብሎ፥

-በሴቷም አካለ ሥጋ ውስጥ፡ በማሕፀኗ ሽል ኾኖ፡ በእግዚአብሔር ዕፁብ ድንቅ ሥራ የሚፈጠረውን፡ ያን፡ ቅዱስና ንጹሕ ዘር ተቀብላ፡ በፍጹም ሰውነት ለመፅነስ፡ የተዘጋጀች መኾኗን የምታበሥርበትን፡ ያን፡ ቅዱሱንና ንጹሑን የወር አበባ፡ "አደፍ፥ ጉድፍ፥ መርገምና ርኵሰት" ብሎ፥

-በቅድስናና በንጽሕና የተሸለሙትን፡ እነዚህኑ የፅንስ አካላትና ባሕርያት የሚያስገኙትን፡ የወንዱንም፥ የሴቲቱንም፡ የሰውነት አባላት፡ "አባለ-ዘር" እና "አፈ-ማሕፀን" ማለት ሲገባ፡ "ኀፍረተ-ሥጋ" ብሎ፤

-"ባል" የተባለው ወንዱ እና "ሚስት" የተባለችው ሴቷ፡ እግዚአብሔር፡ የተቀደሱና የተከበሩ፥ የነጹና ያማሩ አድርጎ በሠራቸው በእየብልቶቻቸው አማካይነት የሚያደርጉትን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት፡ "ኃጢኣት" ብሎ፡ በመፈረጅ፡ በዚያው፡ በክፉ ሰዎች ሰይጣናዊ አስተሳሰብ፡ በጋብቻና የእርሱ በኾኑት የባሕርይ ምግባራት ላይ፡ ለተካኼደውና እየተካኼደ ላለው ዘመቻ፥ ከተፈጸመውና እየተፈጸመ ላለው ጥቃት፡ በቂ ማስረጃ ነው።

ስለዚህ፡ "ይኸው 'ሚስት' የሚለው ቅዱሱና ንጹሑ መለኮታዊ ቃል፡ እንደእርስዎ ዘይቤና አጻጻፍ፡ *"አለማዊ ዕሳቤ እን[ዲ]ይዝ"* ለምንና በማንስ ተደረገ?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱ፡ ግልጽና ቀጥተኛ ነው፤ እርሱም፡-

በአንድ ወገን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን፥ የባልና ሚስት ነገርን የያዘውን፡ ሥርዓተ-ጋብቻንና የሴትን ክብር፡ እያንኳሰሰና እያንቋሸሸ፥ እያረካከሰና እየረገመ ከሚያቃልለውና ከሚንቀው፥ ከሚያዋርደውና ከሚያወግዘው፤

በሌላው ወገን ግን፡ ኢእግዚአብሔራዊ የኾነውን አርዑተ-ምንኵስናን እያሞጋገሰና እያከባበረ፥ እያላቀና እያሞካሸ ካገነነውና ካነገሠው፥ ከቀደሰውና ካመለከው ሰይጣናዊ አስተሳሰብ የመነጨው ይትበሃል መኾኑን፡ የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።

ከዚህ የተነሣ፡ መለኮታዊ ሥርዓት የኾነው፡ ራሱ ቅዱሱ ጋብቻ፡ በኦሪታውያኑ አይሁድ ዘንድ ቀርቶ፡ "ክርስቲያን ነኝ!" በሚለው፡ በግብዙ ኅብረተሰብም ዘንድ፡ እንኳንስ፡ ከሠሪው፥ ከፈጣሪው የተቀዳጀውን የቅድስናና የንጽሕና ክብርና ማዕርግ ሊያገኝ፥ የጋብቻው ፈጻሚዎችና ባለቤቶች የኾኑት፡ አዳማዊው ወንዱና ሔዋናዊቷ ሴቷ ጭምር፥ "ባልና ሚስት" ከሚለው መታወቂያ ስያሜያቸው ጋር፡ ይኸው እንዲህ፡ "የህልውና ማፈሪያዎችና የኃጢኣት መገለጫዎች" እስከመባል ደርሰው፡ ኑሮአቸውን፡ በመሸማቀቅ ሲገፉ ይታያሉ።

ይኸ ብቻ አይደለም፤ ከዚህ የተነሣ፡ በክፉው የዓለም ኅብረተሰብ መካከል፡ ከእግዚአብሔርዋ ደግነት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ክፋት፥ ከእግዚአብሔርዋ እውነት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ሓሰት [ኃጢኣት]፥ ከእግዚአብሔርዋ ሕይወት ይልቅ፡ ሰይጣናዊው ሞት፡ በሰዎች ላይ፡ ዐይሎና ሠልጥኖ ሲሠራ እንደሚታይ ኹሉ፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ያልሠራው አርዑተ-ምንኵስናም፡ እንዲህ፡ በክፉ ሰዎች ዘንድ፡ እግዚአብሔር ከሠራውና አክብሮ ከፈጸመው፡ ከሥርዓተ-ጋብቻ በላይ ተከብሮና ተፈላጊ ኾኖ፡ እንደልቡ ሲገዛና ሲነዳ ይታያል።

በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ ግን፡ የጋብቻ፥ የባልና ሚስትም ነገር፡ እንዲህ አይደለም፤ ሥርዓተ-ጋብቻ፥ እንዲሁም፡ "ሚስት" እና "ባል" የሚሉት፡ ከእርሱ ጋር የተያያዙት ቃላት፡ ቅዱሱን ጋብቻ እንደሠሩትና እንደፈጸሙት፥ ደግሞም፡ የዚሁ የጋብቻ መገለጫዎች የኾኑትን፡ ቅዱሱን አዳምና ቅድስቲቱን ሔዋን፡ "ከእኛ፡ እንደአንዳችን ኾኑ!" ብለው እንደፈጠሩት፡ እንደእግዚአብሔር እም እና እንደእግዚአብሔር አብ፡ የተቀደሱና የተከበሩ፥ የተወደዱና የተመረጡ ኾነው፡ ለዘለዓለም የሚኖሩ ናቸው።

እንዲህ፡ በእርስዎና በመሰሎችዎ ዘንድ፡ ሊኖር ለሚችለው፡ ለዚህና ለሌላው፡ እጅግ ብዙ ለኾነው፡ እንደዚህ ላለው፡ የተያያዘ ጥያቄና ትች ኹሉ፡ አጥጋቢ መልስና በቂ ማብራሪያ ይኾን ዘንድ፡ በጽሑፍ የተሰጠው ዝግጅታችን፡ በጎዋ ሰሌዳችን፥ እንዲሁም፡ በፌስ ቡክ፥ በዩ-ቲዩብና በሳውንድ መድረኮቻችን፥ ዝርዝራቸውም፡ በእነዚሁ መድረኮቻችን ላይ ሠፍሮ በሚነበበው መጽሓፎቻችን ውስጥ ስለሚገኝ፡ እባክዎ ያንን ይመልከቱ!?

ይህን የጨዋነት ምግባር በመፈጸም፡ የእርስዎንና የእኛን ውድ ጊዜ ማዳን ብቻ ሳይኾን፡ ከዚህ ጋር፡ በእርግጥ፡ ስለእግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት እውነት፡ የማወቅ ፍላጎት ካለዎ፥ ያም ፍላጎትዎ፡ እውነተኛ ከኾነ፡ ያን ፍላጎትዎን፡ በበለጠ ሊያረኩ እንደሚችሉ እናምናለን።

\+ \+ \+

**ከመልክዐ ሲራክ የቀረበ ትች፡-**

*የሰለሞን ምስት ኢትዮጵያዊነት በምን ታወቀ ብትሆንስ ከሠሎሞን በኋላ የተሰረዘው የተደለዘው የተበረዘው ትውልድ እስራኤላዊነት አይፀናበትምና ነው ከ40 የትውልድ ጅረት በኋላ ኢትዮጵያዊነቱ ገኖ እስራኤላዊነቱ ኮሶ ክርስቶስ የተወለደው? እስኪ እንደው እንዴት አይነት የለየልን ትል ራሶች ብንመስላቹህ ነው እንዲህ ሆድና ጀርባ የሆነ ታሪክ እየነገራቹህ ልታሣምኑን የምትዳዱት? በናንተ ቤት ከናንተ በላይ የሚያስብ የለም አይደል?*

**ከኢእመ የተሰጠ መልስ፡-**

ይድረስ፡- ለአቶ መልክዐ ሲራክ!

ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ በእግዚአብሔር አብወእም ስም እያቀረብንልዎ፡ ስለሰሎሞን ምሽት ኢትዮጵያዊነት ለሰጡት የምፀት ትች፡ የምንሰጥዎ መልስ፡ "እግዜር ይስጥልን!" ከሚለው አጻፋችን ጋር፡ ባጭሩ፡ ከዚህ የሚከተለው ነው።

እርስዎ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፥ በእምነቷና በትምህርቷም የማያምኑ ከኾኑ፥ ወይም፡ ስለእርሷ፥ ስለእምነቷና ስለትምህርቷም፡ በቀጥታ፡ ከእርሷው ለማወቅ የማይፈልጉ ከኾኑ፡ ለምን፡ ወደዚህ መድረካችን በመምጣት ይደክማሉ? ለምን፡ እዚያው፡ በሚከተሉትና አባል በኾኑበት የሃይማኖት ድርጅትዎ አይወሰኑም?

አዩ! የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የእናቱ ኢትዮጵያ ድንግል ማርያም ልጅ፤ የእኛም የኪዳናውያትና የኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆች መሪና መምህር የኾነው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ስለእርስዎና እርስዎን ስለመሰሉት ኹሉ፡ እንዲህ ሲል የተናገረውን ሰምተዋል? አንብበዋል? **"ዘሰ እምእግዚአብሔር ውእቱ፡ ቃለ-እግዚአብሔር ይሰምዕ። ወበእንተ ዝንቱ፡ አንትሙሰ፡ ኢትሰምዑኒ፤ እስመ ኢኮንክሙ እምእግዚአብሔር።**

"ከእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል። እናንተ ግን፡ ከእግዚአብሔር ስላልኾናችሁ፡ ስለዚህ፡ አትሰሙኝም።" (ዮሐ. ፰፥ ፵፯።)

ይኾን እንጂ ደግሞ፡ በእርግጥ፡ ስለእግዚአብሔርና ስለኢትዮጵያዊነት እውነት፡ የማወቅ ፍላጎት ካለዎ፥ ያም ፍላጎትዎ፡ እውነተኛ ከኾነ፡ ያን ፍላጎትዎን፡ በበለጠ ሊያረኩ የሚችሉበት መንገድ አለልዎ፤ ይኸውም፡እንዲህ፡ በእርስዎና በመሰሎችዎ ዘንድ፡ ሊኖር ለሚችለው፡ ለዚህና ለሌላው፡ እጅግ ብዙ ለኾነው፡ የተያያዘ ጥያቄና ትች ኹሉ፡ አጥጋቢ መልስና በቂ ማብራሪያ ኾኖ፡ በጽሑፍ የተሰጠው ዝግጅታችን፡ በኅዋ ሰሌዳችን፥ እንዲሁም፡ በፌስ ቡክ፥ በዩ-ቲዩብና በሳውንድ መድረኮቻችን፥ ዝርዝራቸውም፡ በእነርሱ ላይ ሠፍሮ በሚነበበው መጽሓፎቻችን ውስጥ ስለሚገኝ፡ እባክዎ ያንን ይመልከቱ!? ይህን የጨዋነት ምግባር በመፈጸም፡ የእርስዎን ብቻ ሳይኾን፡ የእኛንም ውድ ጊዜ ሊያድኑልን ይቻልዎታል።

\+ \+ \+